# ያልተፈታው ሕልሜ

አሥራደው ( ከፈረንሳይ )

የውስጤ ወላፈን የውስጤ ትኩሳት ፣
የመሆኔ ትርጉም የኔነቴ መብራት ፣
የቆየ ሕልም አለኝ ውሉ ያልተፈታ ፣
የሚነተጉተኝ ሁሌ ጠዋት ማታ ፣
የሚቀሰቅሰኝ ለሊት ከመኝታ ::

ብልጭ ቦግ ሲል ፣
ሲነድ ሲቃጠል ፣
አጥንት ሲለበልብ ፣
ቆዳ ሲሸበሽብ ፣
ጅማት ሲያገነትር ፣
ቀለም አሰለውጦ ሲያሸሽ የራስ ጠጉር ፣
ይታያል ከፊቴ ፣
መጉላላት መክሳቴ ፣
ታምቆ ብርታቴ ትርጉም የድርጊቴ ::

የቆየ ሕልም አለኝ ውሉ ያልተፈታ ፣
የተነናነነ የውስጤ ቅሬታ ፣
በውስጤ እሚጉላላ ፣
ተጉላልቶ እሚያጉላላ ፣
ታምቆ ብርታቴ ፣
ትርጉም የድርጊቴ ፣
ይታያል ከፊቴ ፣
እሮሮ ሲያሰማ በሠራ አከላቴ ::

የሚፈታ አልሻም ፈቺው እራሴ ነኝ ፣
ግን ፣
አላላውስ ብሎ ደንቃራ ሆኖብኝ ፣
እያደናቀፈ እየኮረኮመኝ ፣
እንዳልተረጉመው ጊዜ ከለከለኝ ::

በሠራ አከላቴ እየተወራጨ ፣
በልሜ አለመፈታት እድሜዬ ቀጨጨ ፣
ወዘናዬ ጠፍቶ መልኬ ተለውጦ አጥንቴ ደረቀ ፣
ከኔው እየሸሸ እኔነቴ ራቀ ::

አድጎ እንዳያሳድግ ዕውቀት በድርጊቴ ፤
በውስጤ ታምቆ ሃይልና ብርታቴ ፤
የሕሊና ክብሪት ወቀሳ እየጫረ ፤
አካሌን በሙሉ እየመረመረ ፤
ምን ሠራህ ?! ይለኛል ፤
ሁሌ በወቀሳ ይደቋቁሰኛል ::

ለሊት ከመኝታ የሚቀሰቅሰኝ ፤
ውሉ ያልተፈታ የቆየ ሕልም አለኝ ፤
ነዶ የሚያቃጥል ፤
ከስሎ የሚያከስል ፤
አይምሮ የሚንድ ልብ የሚሸረሽር ፤
አካል ማገዶ አርጎ ነብስ የሚያንጨረጭር ፤
የውስጤ ትኩሳት የውስጤ መንጨርጨር ፤
ለወገኔ ስቃይ ለወገኔ ችገር ፤
ሆኜ በመቅረቴ አቅመቢስ ባለአገር ፤
የትውልድ ባለዳ የማይመልስ ብድር::

አንተም እንደኔ ነህ ?
ውሉ ያልተፈታ የቆየ ሕልም አለህ ?
ዘወትር ጧት ማታ ሁሌ እሚሞግትህ ፤
ምን ሠራህ ላገርህ ?!
ምን ፈጠርክ ?! እያለ የሚጎተጉትህ ::

አንቺስ እህት ዓለም ፤
አለሽ የቆየ ሕልም ?
የተጎናጎነ ውሉ ያልተፈታ ፤
ተጉላልቶ እሚያጉላላ የውስጥሽ ቅሬታ ፤
እወልዳለሁ ብለሽ በፍቅር የጸነስሺው ፤
ሽል ሆኖ የቀረ ያልተገላገልሽው ::

ጥቅምት 20  2001 ዓ.ም